https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 13
ADDIS ABABA 21st December,2018

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፵፩/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.....ገጽ ፲ሺ፯፻፳፩

Content

Regulation No. 441/2018

Definition of Power, Duty and Organization of the Basin Development Authority Regulation.....Page 10721

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፩/፪ሺ፲፩

የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣንን ሥልጣን ፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፯፻፺/፪ሺ፲፩ አንቀጽ (፭) እና አንቀጽ (፴፬) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

፩/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፪/ "ውሃ" ማለት የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ ነው፡፡

፫/ "ተፋሰስ" ማለት ወደ አንድ መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ነው፡፡

council of ministers regulation no. 441/2018

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DEFINE THE POWER, DUTY AND ORGANIZATION OF THE BASIN DEVELOPMENT AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Power and Duty of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018.

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Definition of Power, Duty and Organization of the Basin Development Authority Regulation No. 441/2018."

2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Minster" or "Ministry" means the Minster or Ministry of the Ministry of Water, Irrigation and Energy respectively;

2/ "Water" means surface water and ground water;

3/ "Basin" means a geographical area described by the watershed limits of water system including surface water and ground water flowing into a common terminus;

https://chilot.me

፬/ "ባለስልጣን" ማለት የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ማለት ነው፡፡

፭/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማናቸውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

፮/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

፫. <u>የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፎች ሊኖረው ይችላል፡፡

፬. <u>ዓላማ</u>

የባለስልጣኑ አጠቃላይ ዓላማ ዘለቄታዊና የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም ፍትሐዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ በተፋሰስ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል፡፡

፭. <u>የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባራት</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ይተገብራል፣

፪/ በተፋሰሶች ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፫/ በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

4/ "Authority" means Basin Development Authority;

5/ "Regional State" means any regional state specified under Article 47(1) of the Constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

6/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Head Office</u>

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branches elsewhere as may be necessary.

4. <u>Objective</u>

The overall objective of the Authority shall be to implement sustainable and integrated development, administration and utilization of the water resources at a basin level in equitable and participatory manner.

5. <u>Power and Duties of the Authority</u>

The Authority shall have the following power and duties:

1/ undertake policy studies, surveys and researches needed to create a conducive environment for the implementation an integrated water resource management within basins; and follow up implementation upon approval by the relevant body;

2/ facilitate and undertake activities necessary for implementation of integrated water resources management in basins;

3/ ensure that projects, activities and interventions related to water in the basins are, in line with the integrated water resources management process;

https://chilot.me

፬/ የተፋሰሶችን ጥበቃና ዘላቂ ጥቅም በተመለከተ እቅድ ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፭/ የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ እቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤

፮/ ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ይለያል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤

፯/ ለክልሎች በህግ የተሰጠ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሶች ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል አግባብ ባለው ህግ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል፣ በፈቃዱ ላይ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

፰/ በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ መስፋፋት ስራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፱/ የወንዝ አቅጣጫ አመራር ስራ ይሰራል፤

፲/ በተፋሰሶች የሚገኘውን የውሃ ሃብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደር እና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያጠናቅራል፤ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

፲፩/ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ለሚኒስቴሩ ተገቢውን የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪/ ከክልል መንግሥት አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፲፫/ ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ከሌሎች አገሮች ጋር ለመወያየት አግባብ ላለው አካል አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤

4/ develop plans for protection and sustainable uses of basins; follow-up implementation once it is approved by the relevant organ;

5/ develop and implement basin models in order to guide and support strategic planning of water resources and water administration functions;

6/ Identify measures that should be taken against pollution and damage to basins; implement same in collaboration with relevant organs;

7/ without prejudice to the power given to Regional States by law, issue permits applicable to the basins' water use and water works, and ensure that the terms of the permits are complied with;

8/ work in collaboration with relevant organs to support efforts to expand irrigation works within basins;

9/ undertake administration of river training activity;

10/ measure, collect, compile, analyze and disseminate information for proper planning, administration and steering of water resources in the basin;

11/ give advice and technical support to the Ministry of Water, Irrigation and Energy on dispute resolution in relation to the allocation and use of water resources of the basins;

12/ ensure continuous collaboration with Regional Governments organs and other relevant bodies by setting up a forum for effective networking;

13/ Prepare and provide necessary information on trans-boundary basins to the concerned body in charge of negotiations with other countries;

https://chilot.me

፲፬/ የተፋሰስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ይመሠርታል፤ ያስተዳድራል፤

14/ Develop and manage basin information system;

፲፭/ የተቀናጀ የተፋሰስ መሪ እቅድ ያዘጋጃል፤ ይከልሳል፣ ሲፀድቅም ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

15/ Prepare and update basin master plans; implement and support the implementation of the same upon approval;

፲፮/ የተፋሰሶችን የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር እቅድ ያዘጋጃል፣ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

16/ Prepare basin development and management plans, submit the plan to the Ministry, follows up the implementation of the plans up on approval;

፲፯/ የውሃ አካላትንና ተያያዥነት ያላቸውን ስነምህዳሮች ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤

17/ Conserve, protect and manage water bodies and related ecosystem.

፲፰/ የጎርፍ መከላከያ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራን ያከናውናል፣ ከጎርፍ እና ከድርቅ ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የሰዎችና የእንስሳት ህይወት እና ንብረት ከአደጋ ለመታደግ አግባብነት ካለቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን ያከናውናል፤

18/ Study and implement flood protection forecasting and early warning works. Protect and save lives and properties in case of flood and drought, by implementing various flood protection and drought mitigation measures in coordination with relevant bodies;

፲፱/ ከአንድ በላይ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይንም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ አገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ጥናት ያዘጋጃል፤ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

19/ prepare and submit to the ministry means of optimal and equitable allocation and utilization of water bodies that traverse across or lie between more than one regional state among various uses and regional states.

፳/ ድንበርና ድንበር ዘለል ወንዞችንና የከርሰ-ምድር የውሃ ሀብቶችን ፍትሐዊ፣ ህጋዊና ዘለቄታዊ አጠቃቀም" ያጠናል፣ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ የዓለም አቀፍ ውሎችን በተመለከተ የድርድር ምክረ-ሃሳቦችን ያቀርባል ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

20/ Study, generate policy ideas, follow-up the implementations of the equitable and sustainable utilizations and management of the trans-boundary and boundary rivers, lakes and aquifers;

፳፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

21/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

፳፪/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

22/ Carry out other functions necessary for the implementation of its objective.

https://chilot.me

፮. <u>የባለስልጣኑ አደረጃጀት</u>

ባለስልጣኑ፤

፩/ በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ፣እና

፪/ አስፈላጊው ስራተኞች ይኖሩታል፡፡

፯. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባራት</u>

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ ስራ አስፈጻሚ በመሆን የባለስልጣኑን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ (፭) የተመለከቱትን የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የባለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለስልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፤

መ) ለባለስልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለስልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለስልጣኑን የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለስልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፰. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባራት</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ:-

፩/ የባለስልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

6. <u>Organization of the Authority</u>

The Authority shall have:

1/ A Director General and Deputy Director Generals, as may be necessary, to be appointed by the Government, and

2/ the necessary staff.

7. <u>Power and Duties of the Director General</u>

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority shall direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without Prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the power and duties of the Authority specified in Article (5) of this Regulation;

b) employ and administer the employees of the Authority in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare annual work plans and budgets of the Authority and implement the same upon approval;

d) effect payments in accordance with approved budget and work program of the Authority;

e) represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) submit to the Ministry performance and reports of the Authority.

3/ The Director General may delegate part of his power and duties to employees of the Authority to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Authority.

8. <u>Power and duties of the deputy director Genral</u>

The deputy director general shall:

1/ assist the Director general in organizing, directing and coordinating the activities of the Authority;

https://chilot.me

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጠውን የሥራ ዘርፍ ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

፱. በጀት

የባለስልጣኑ በጀት በፌደራል መንግሥት ይመደባል፡፡

፲. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ባለስልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ ሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒሰትር

2/ perform duties specifically assigned to him by the Director general;

3/ Act on behalf of the Director General in his absence.

9. Budget

The Authority budget shall be allocated the Government.

10. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an Auditor designated by him.

11. Effective Date

This Regulation shall come into force on the date 14th November 2018 as endorsement by the Council of Ministers.

Done at Addis Ababa this 21st day of December ,2018

ABIY AHMED (DR.)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA